

# መታዘዝ የበረከት ምንጭ ነው

15-2

## አለመታዘዝ ጥፋትን ያመጣል

1. እሥራኤላውያን ወደ ተስፋው ምድር ሲገሰግሱ አማሌቃያን በራፊድም ጦርነት ገጠሟቸው። በመደጋገም አማሌቃውያን የእሥራኤልን ሕዝብ የሚያስጨንቁ ጠላቶች እንደነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (ዘዳ. 25፥17-19)። የእሥራኤል ሕዝብ በአማሌቃውያንና በፍልስጥኤማውያን እጅ ተራ በተራ ተጠቃ። ተደጋጋሚ መጠቃት ከጠላቶቻቸው ሲደርስባቸው እግዚአብሔር አውቆ እንጂ ሳያውቅ አይደለም። ፍርድ ለጊዜው ይዘግይ እንጂ በማይታዘዙት ላይ መድረሱ የማይቀር ነው።

2. እግዚአብሔር ለሳኦል እንዲህ የሚል ትዕዛዝ ሰጥቶት ነበር። "ሄደህ አማሌቅን ምታ ያላቸውንም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋ፤ አትማራቸውም፤ ወንዱንና ሴቱን፣ ብላቴናውንና ሕጻኑን፣ በሬውንና በጉን፣ ግመሉንና አህያውን ግደል" የሚል ነበር (ሳሙ ቀዳ 15፥3)። ሳኦል በእግዚአብሔር እርዳታ አማሌቃውያንን መታ፤ ፍጹምም አጠፋቸው። ይሁን እንጂ የታዘዘውን ትዕዛዝ በሙሉ አልፈጸመም። ለንጉሡ ለአጋግ ለተመረጡትም በጎችና በሬዎች ለሰቡትም ጥጆችና ጥቦቶች ለመልካሞ ቹም ሁሉ ራሩላቸው፤ ፈጽሞ ሊያጠፋቸው አልወደደም። ነገር ግን ምናምንቱንና የተናቀውን ሁሉ ፈጽመው አጠፉት" (ሳሙ ቀዳ 15፥ 8-9)። በከፊል ብቻ እግዚአብሔርን መታዘዝ እንዳልተመዘዝ ይቆጠራል። አማሌቅ በሥጋዊ ኃጢአት ይመሰላል። ይህንንም ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ ኦፕራ ሲዮን (ቀዶ ጥገና) ያስፈልገዋል። አለበለዚያ ሁኔታውን አይለውጠውም። "እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚ ኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና፤ እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ። ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና መገዛትም ትስኖታል በሥጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም" (ሮሜ 5፥8)።

3. ነብዩ ሳሙኤል በሳኦል ላይ በደረሰው ሁኔታ ልቡ ተሰበረ፤ አዘነ። እግዚአብሔር ሳሙኤልን እንዲህ አለው "ሳኦልን ንጉሥ በማድረጌ ተጸጽቻለሁ፤ ፊቱን ከእኔ መልሷል፤ ትዕዛዜንም ሰብሮአል" አለ። በዚህም ሳሙኤል አዘነ፤ ወደ ጌታም ለሳኦል እየማለደ ሌሊቱን ሁሉ ጸለየ።

4. ሳኦል የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ፈጽሜአለሁ ቢልም እግዚአብሔር ግን "አልፈጸምክም" ይለዋል። የሳኦልን ድርጊት ትክክል እንደሆነ የሚያምኑ፥ ሳኦል የሰቡትን በጎችንና አህዮችን ያላጠፋው ለበጎ ነገር ስለሆነ እንደ መተላለፍ አይቆጠርበትም" ይላሉ።

5. ሳሙኤል እንዲህ አለው "በውኑ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ደስ እንደሚለው እግዚአብሔር በሚቃጠልና በሚታረድ መስዋዕት ደስ ይለዋልን? ዓመጸኛነት እንደ ምዋርተኛ ኃጢአት እልከኝነትም ጣኦትንና ትራፊንም እንደማምለክ ነው።" የሳኦል ተደጋጋሚ መተላለፍ እግዚአብሔርን አስቆጣ። ሳኦል ንስሃ ቢገባም ከእውነተኛ ልብና መንፈስ የመነጨ አልነበረም። ይሁዳ ጌታውን በ30 ብር አሳልፎ ሲሰጥ በኃዘን ልቡ ተሞልቶ "ንጹህ ደም አሳልፌ ሰጠሁ" አለ። ይሁን እንጂ በተሠበረ

ልብ ያቀረበው የንስሃ ጸሎት አልነበረም። ዳዊት ግን “ኃጢአቴን ለአንተ አስታወቅሁ፤ በደሌንም አል ሸፈንሁም፤ ለእግዚአብሔር መተላለፌን እነግራለሁ” ይላል (መዝ 32፥5)። ሶል እግዚአብሔርን ባለ መታዘዙ መንግሥቱን አጣ፤ እኛም ከአምላክ ፈቃድ ውጪ ስንኖር የዘለለምን ሕይወት እናጣለን።

## መታዘዝ

1. በብሉይ ኪዳን “መታዘዝ” ከፍተኛ ሥፍራ አለው። አለመታዘዝ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ያለውን ቅርብ ግንኙነት ያፈርሳል። አብርሃም እግዚአብሔርን በመታዘዙ ለብዙዎች በረከት ሆነ።

   እግዚአብሔርን አውቀዋለሁ እያለ የእርሱን ትዕዛዞች የማይፈጽም ቢኖር ሀሰተኛ ነው፤ እውነት በእርሱ ውስጥ የለም። ለእግዚአብሔር ቃል የሚታዘዝ ሁሉ ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር ፍጹም ነው፤ የክርስቶስ መሆናችንም የሚታወቀው በዚሁ ነው” (1ኛ. ዮሐ 1፥4-5)።

   እሥራኤል የእግዚአብሔር የተመረጠ ሕዝብ መሆን የሚችሉት በመታዘዛቸው ነው (ዘጸ 19፥5)።
   በመታዘዝ በረከት፥ ባለመታዘዝ ፍርድ አለ (ዘዳ 11፥26-28)
   የእሥራኤል ሕዝብ በበረሃ መንከራተት ባለማመናቸውና ባለመታዘዛቸው ምክንያት ነው (ኢያሱ 5፥6)።

2. አለመታዘዝ ኃጢአት ነው። (ኤር 3፥25፤ 40፥3) እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ችላ ያለ፥ እግዚአብ ሔርን ችላ ይለዋል። መታዘዝ ከመስዋዕት ሁሉ ይበልጣል።

3. መታዘዝ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ አለው። ክርስቶስ አባቱን ሙሉ በሙሉ ታዘዘ፤ በመ ታዘዙም ወደ መስቀል ሞት ተነዳ (ሮሜ 5፥19 ፊሊጵ 2፥8)። የክርስቶስ ለእግዚአብሔር ፈቃድ መታዘዙ እኛን ክርስቲያኖችን ከመታዘዝ ኃላፊነት ነጻ ያወጣናል ማለት አይደለም።

መታዘዝ ግዴታችን ነው።

እግዚአብሔርን ታዘዙ (ዘዳ 13፥4)

የክርስቶስን ትዕዛዝ ጠብቁ (ዮሐ 14፥15)

ክርስቲያን ጌታውን ለመታዘዝ የተመረጠ ነው (1ኛ ጴጥ 1፥2)

መታዘዛችን እግዚአብሔርን የማወቃችን ምልክት ነው (1ኛ ዮሐ 2፥3 ና 4)

በመታዘዛችን የምንለምነውን ሁሉ ከእርሱ እናገኛለን (1ኛ ዮሐ 3፥22)

በመታዘዛችን ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር ይለካል (1ኛ ዮሐ 5፥2 ና 3)

መታዘዛችን ከልብ መሆን ይገባዋል (ሮሜ 6፥17)

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። እሜን!**